

## የአገራችን ሚድያ ህገ መንግስታችን እንዲከበር ግንባር ቀደም ሚናዉን ይጫወት

ጎይትኦም ጊጋር   09-20-17

መቐለ፣

በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ትልቅ ትኩረት እያገኙ ካሉት ማህበራዊ ዘርፎች አንዱ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ እንደሆነ ይታወቃል። መንግስታት፣የፖለቲካ ድርጅቶች እና ፋብሪካች እንዲሁም ግለሰቦች ሳይቀር የቆሙለትንና ያነገቡትን ኣላማ፣ራእይ፣ተልእኮ እና ምርቶቻችዉ ከተጠቃሚዉ ማህበረሰብ ጋር ለማስተዋወቅ ሁነኛ መሳርያ አድርገዉ የሚጠቀሙት የህዝብ ግንኙነት ስራ አንዱና ዋነኛዉ ነዉ።

የምንገኝባት አለም የሰዉ ልጆች በመረጃ እርስ በርስ የተሳሰሩበት የኢኮኖሚ፣ማህበራዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንደ ሸረሪት ድር ተቆራኝተዉ የሚገኙበት የሉላዊነት ወይም ግሎባላይዜሽን ዘመን እንደሆነ ግልፅ ከሆነልን ዉለን አድረናል ብቻ ሳይሆን ራሳችን በዚህ የዉድድር ዘመን አስገብተን ላለመሸነፍ ወይም በቁም ላለመሞት የሞት ሽረት ትግል የምናደርግበት አለም ዉስጥ ነዉ ያለነዉ።በዚህ የዉድድር አለም ሁሉም መንግስታት የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም የንግድ ድርጅቶች መረጃቸዉን በፍጥነት ወደ ማህበረሰቡ ለማድረስ የህዝብ ግንኙነት ስራቸዉን በተሳካ ሁኔታ መከወን የሚችሉት በሚመርጡት ስልት ወይም ጥበብ ይሆናል።ይህ ማለት ወደ ማህበረሰቡ ለመድረስ የሚያስችላቸዉ እና እንደ ድልድይ የሚያገለግላቸዉ ሚድያ ይመርጣሉ ማለት ነዉ። ከዚህ በመነሳት አንዳንዶቹ ሬድዮ ሲመርጡ ሌሎቹ ደግሞ ቴሌቪዥን አልያም ዘመኑ ባፈራቸዉ የማህበራዊ ትስስር ኣዉታሮች እንደ ፌስቡክ፣የመሳሰሉትን ይጠቀማሉ።ይህን መምረጥ የሚችሉት ደግሞ የተጠቃሚዉ ማህበረሰብ የእድገት ደረጃ ታሳቢ አድርገዉ የትኛዉ ሚድያ በስፋትና በጥራት መልእክታቸዉ እንደሚያደርስላቸዉ ታሳቢ በማድረግና የሚመቻቸዉን በመምርጥ ይሆናል።

በኣገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ገዢዉ ፓርቲን ጨምሮ ሌሎች ፓርቲዎችም ሆነ የንግድ ተቋማት የተለያዩ ሚድያዎች ወይም የመገናኛ አዉታሮችን ተጠቅመዉ የህዝብ ግንኙነት ስራቸዉን እየሰሩ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በገጠሪቱ ክፍል የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን ይህንን ማህበረሰብ ለመድረስ ሬድዮ ቀዳሚ ምርጫቸዉ ቢሆንም የቴሌቪዥን አገልግሎት ሽፋን

በመጨመሩና የማህበራዊ ሚድያ እድገት በፍጥነት እያደገ በምምጣቱ ሁሉንም አማራጮች እየተጠቀሙ መልእክቶቻቸዉን እያስተላለፉ ይገኛሉ።

ገዢዉ ፓርቲም ሆነ እሱን የሚቃወሙ ፓርቲዎች ፖሊሲዎቻቸዉ እና ፕሮግራሞቻቸዉ በመረጡት ሚድያ መልእክቶቻቸዉ እያደረሱ እደሆነ አንድ ጉዳይ ሆኖ ከነዚህ አካላት ባልተናነሰ ደግሞ ግለሰቦች የራሳቸዉን ዉስጣዊ ስሜትና ፍላጎት አፍራሽ ቅስቀሳም ይሁን ገንቢ በመረጡት የመገናኛ አዉታር ተጠቅመዉ እየገለፁ እንደሚገኙ ግልፅ ነዉ።

የኢፌድሪ ህገ መንግስት ንቀፅ 29 ንኡስ አንቀፅ 2 እንደሚደነግገዉ *"ማንኛዉም ሰዉ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለዉ። ይህ ነፃነት በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በፅሁፍ ወይም* ***<u>በህትመት፣ በሥነ ጥበብ</u>*** *መልክ ወይም በመረጠዉ በማንኛዉም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛዉም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመሰብሰብ የመቀበል የማሰራጨት ነፃነቶች ያካትታል"* ይላል (የተሰመረበት የራሴ)

ከዚህ ድንጋጌ ለመረዳት እንደሚቻለዉ ዜጎች በሀገራቸዉ ጉዳይና ይመለከተኛል በሚሉት አጀንዳ ራሳቸዉ በመረጡት እና በመሰላቸዉ መንገድ ሃሳባቸዉን የመግለፅ መብት እንዳለባቸዉ ያስረግጣል። በሌላ በኩል ይህንን የዜጎች ዲሞክራሲያዊ መብት ይበልጥ ለማጠናከር በህገ መንግስታችን አንቀፅ 29 ንኡስ አንቀፅ 3 ተራ ቁጥ ሀ *የቅድሚያ ምርመራ በማንኛዉም መልኩ የተከለከለ መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል።* ይህንን አንቀፅ በይበልጥ የሚጠቅመዉ በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ለተሰማራዉ ዜጋ የመሰለዉን ሀሳብ ሳይሸማቀቅ በመሰለዉና በመረጠዉ መንገድ ሲያሻዉ በዘፈን፣ሲፈልግ በቀልድ፣በግጥም ወዘተ ሀሳቡን ለመግለጽ የሚያስችለዉ ዲሞክራሲዊ መብትን የሚያረጋግጥለት ነዉ። እንዲህ አይነቱ ዲሞክራሲያዊ መብትን በመጎናፀፋችን ምክንያት ደግሞ ብዙ የኪነ ጥበብ ሰዎች የመሰላቸዉን ሃሳብ በመረጡት መንገድ እየገለፁና ብዙ ተከታይም እያፈሩ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚያቀርቡትን ጭብጥ የህዝቡን ፍላጎት እና ብሶት በማንፀባረቃቸዉ ምክንያት ተደማጭና ተወዳጅነትን ከማትረፋቸዉ በላይ ተፅእኖ ፈጣሪነታቸዉም እየጨመረ የመጡ እንዳሉ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ።

ይህንን ፅሑፍ እንድፅፍ ያነሳሳኝ ዋናዉ ቁምነገር የአገራችን የሚድያ አወታሮች በተለይ ደግሞ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩትም ሆነ ከመንግስት ፍቃድ አግኝተዉ የተከፈቱትን ሁሉም ሚድያዎች ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርጉ የሚያስተላልፉዋቸዉን ክሊፖች እና እንድምታቸዉን ለመጠቆም እና ስህተታቸዉን እንዲያርሙ ለማድረግ እንጂ እነዚህ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች ሂስ ለማድረግ አልያም እነሱን ለመኮነን አይደለም።

እርግጥ ነዉ በአገራችን ያሉ አብዛኞቹ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች ህዝቡን በፀረ ድህነት ትግሉ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ፣ ለልማት እንዲነሳሳ፣ ከኃላቀርነትን እንዲላቀቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ

እያደረጉ እንዳሉ ሁሉ በጣም ጥቂቶች ደግሞ የራሳቸዉን ጥቅም ብቻ በማየት አልያም እንወክለዋለን የሚሉትን የአንድን ብሄር፣ ከብሄርም አለፈዉ የአንድ አከባቢ ህዝብ የበላይነትን ለማሳየት የሚያደርጉትን ቅስቀሳ ህዝብን ከህዝብ ጋር በማጋጨት የአገራችንን አንድነት አደጋ ዉስጥ የሚከት መልእክት የሚያስተላለፉ እንዳሉ ግልፅ ነዉ። እነዚህ በጣም ጥቂት አርቲስቶች የሚያስተላለፉት መልእክት አደገኛ ቢሆንም በመዝፈናቸዉና ክሊፕ በመስራታቸዉ ግን በእነሱ ላይ ሂስ ማድረግ አልፈልግም። ምናልባት አስፈላጊ ከሆነ ስለ እነሱ በሌላ ግዜ አስተያየት መስጠት እችላሎህ።

ወደ ዋናዉ አጀንዳዩ ስመለስ የአገራችን የመገናኛ አዉታሮች ከተሰጣቸዉ ተልእኮና በህገ መንግስቱ ዙርያ ብሄራዊ መግባባትን እንዲጎለብት መጫወት ከሚገባቸዉ ሚና አንጻር ትኩረት በማድረግ ነዉ።ሁላችንም እንደምንታዘበዉ እነዚህ ጥቂት የሚባሉት አርቲስቶች ኑሯቸዉ በዉጭ አገር ያደረጉ "በዉስጥም እንዳሉ ሳልዘነጋ" የሚሰሯቸዉ ዘፈኖች በዉስጡ ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጩና አንድነታችን የሚያናጉና እርስበርሳችን እንድንጠራጠርና እንድንናቆር የሚያደርጉትን ዘፈኖቻቸዉ በግልፅ አደባባይ በሚጠሩት የሙዚቃ ኮንሰርት የኢትዮጵያን መለያ ያልሆነዉን ሰንደቅ አለማ በመያዝና በማዉለብለብ የሚያቀርቡትን ዝግጅት በመንግስት በጀት በሚተዳደረዉ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ወይም መንግስት በሰጣቸዉ ፍቃድ የሚንቀሳቀሱትን የመገናኛ አዉታሮች ሲተላለፍ ማየት በእጅጉ አሳሳቢም አሳዛኝም ስለሆነብኝ ነዉ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ አለማ በህገ መንግስታችን አንቀፅ 3 ምን አይነት እንደሆነ በማያሻማ መልኩ የተቀመጠ ብቻ ሳይሆን መንግስት በዚህ ሰንደቅ አላማ ብሄራዊ መግባባትን ለመፍጠርና ህዝቡ ሰንደቅ አለማዉን እንዲያከብርና ለባንዴራዉ መስዋእት እንዲሆን በዚህም አገራዊ ፍቅሩንና አንድነቱን እንዲያጠናንክር በማሰብ ብሄራዊ የሰንደቅ አለማ ቀን በአመት አንዴ እንዲከበር በአዋጅ በመደንገግ ለተከታታይ 9 አመታት ማክበሩንና በዙርያዉ ብሄራዊ መግባባር እየገነባ በሚገኝበት ወቅት እነዚህ የአገራችን የመገናኛ አዉታሮች ግን በግላጭ እኛን የማይወክል ሰንደቅ አለማ በአደባባይ ብዙ ህዝብ ጠርተዉ በሚያደርጉት የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ ሲዉለበለብ የሚያሳይ የቪድዮ ክሊፕ በቴሌቪዥን መስኮት ለህዝቡ ማቅረብ ምን የሚሉት እብደት እንደሆነ ሊገባኝ አልቻም። መንግስትስ እንዲህ ለሚያደርጉ አመራሮችና ሰራተኞች እንዴት ዝም ብሎ እንደሚያልፋቸዉ ሊገባኝ አልቻለም።

በቅርቡ በመቐለ ከተማ የተደረገዉ የአማራና የትግራይ ህዝብ ተወካዮች ስብሰባ ከተሳታፊዎች ይነሳ የነበረዉ ሃሳብ አንዱ አንዳንድ ዘፋኞች በሚያቀርቡዋቸዉ ዘፈኖች አንድነታችንን የሚያናጋና እርስ በርሳችን ለማጋጨት ሙከራ እያደረጉ እንደሆነና መንግስት አስፈላጊዉን እርምት ማድረግ እንዳበት በግልፅ ቋንቋ እንዳስቀመጡት የሚታወቅ ነዉ።በዚህ ስብሰባ የተነሳዉ ሃሳብ በእጅጉ ጥልቀት የነበረዉና እነዚህ ጥቂት የሚባሉ አርቲስቶች የሚያስተላልፉት መልእክት ህዝቡን እርስበራሱ እንዲጠራጠርና እያጋጩት እንደሆነ አስምረዉበታል።ይሁን እንጂ መንግስታችንም ይሁን በዚህ

ስብሰባ ተሳታፊ የነበሩትን የሚድያ አካላት ልብ ያሉት አልመሰለኝም። ምክንያቱም አሁንም ድረስ እነዚህ አዉታሮች ተመሳሳይ ይዘት ያለባቸዉ ዘፈኖችና ክሊፖች በሚድያዉ በተደጋጋሚ እያስተላለፉት ይገኛሉና።

ስለዚህ የኢትዮጵያ የመገናኛ አዉታሮች እፊታችን የሚከበረዉ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ቀን ዋና አለማዉ ብሄራዊ መግባባትን መፍጠርና አንድነታችን የምናጠናክርበት ቀን ነዉ እና ይህንን ታሳቢ በማድረግ ለአድማጭ ህብረተሰብ የምታሳዩት የቪድዮ ክሊፖች እና ተቀርፀዉ የሚቀርቡትን የኪነ ጥበብ ዉጤቶች ወደ ህዝቡ ከማድረሳቸዉ በፊት በጥንቃቄ አስተዉለዉ እና የሚኖራቸዉ እንድምታ ተገንዝበዉ ማቅረብ እንዳለባቸዉና በዚህም ህገ መንግስቱ እንዲተገበርና ብሄራዊ መግባባትን እንዲጎለብት የበኩላቸዉ ሚና መጫወት እንዳለባቸዉ አዉቀዉ ኃላፊነታቸዉ ሊወጡ ይገባል። ይህንን ከመተግበር አኳያ ደግሞ በግንባር ቀደምትነት የኢ.ቢ.ሲ፣ዋልታ፣ፋና፣የክልል ሚድያዎች እንዲሁም እንደዚህ አይነት ዘገባዎች በስፋት የሚያቀርበዉ ኢ.ቢ.ኤስ አብነታዊ ሚናቸዉ ሊወጡ ይገባል። መንግስትም መከታተልና እርምጃ መዉሰድ ይጠበቅበታል።

ሳጠቃልለዉ የአገራችንን አንድነት የሚሸረሽሩና እርስበራሳችን በጥርጣሬ አይን እንድንተያይ የሚዳርጉንን ድርጊቶችና ቅስቀሳዎች በማስተዋል እና ሚዛናቸዉ እንዲጠብቁ በማድረግ ለአገራዊ አንድነታችን እንዲሁም ለሰንደቅ ኣላማችን ተገቢዉን ክብር በመስጠት ሁላችንም ለአገራችን ዘብ እንቁም እላለሁ።

መልካም የሰንደቅ አላማ ቀን